# ያልገባን ምን ነው?

ከመይሳው

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች መሀከል የሚታየው አለመግባባትና መከፋፈል ከተፈጠረ ወዲህ ብዙሀኑ ከትግሉ ቢርቁም ጥቂቶች ግን ትክክለኛ ነው ብለው ወዳመኑበት ጎራ (ቡድን) በመቀላቀል ሰንዝር መጓዝ የተሳነው ደካማ የሆነ ትግል መሳይ ጉዞ ከጀመረ ወለው አድረዋል፡፡ እዚህ ላይ በጣም የሚያሳዝነው ግንባር ቀደምና ዋንኛው ጠላታችን (የኢትዮጵያ ጠላት) ወያኔን መታገል መሆኑ ተረስቶ አብዛኛውን ኃይላችንን የምናባክነው እርስ በርስ በመካሰስና በመወነጃጀል አልፎ ተርፎም ኢትዮጵያዊ የሆነውን ወገናችንንና ኢትዮጵያዊውን ድርጅት ስም በማጥፋት አንዱ አንዱን ለማጥፋት የሚደረገው ርብርቦሽ ነው፣ ይህም ለወያኔ ጡንቻ ለተቃዋሚው ክስረትና ድክመት ስለሆነ ሳንወድ በግድ የኃይል ሚዛኑ ወደ ጠላት ጎራ እንዳዘነበለ ልንውጠው የተገደድንበት የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ነው፡፡

እዚህ ላይ ለአንባቢዎች ግልጽ እንዲሆን የምፈልገው ጸሀፊው የማንንም ወገን ለመንቀፍ ፍላጎት ኖሮት ሳይሆን እንደ ማንኛውም አገሩን አፍቃሪ ኢትዮጵያዊ የተገነዘበውን እውነታ ለአንባቢዎች ለማካፈል ነው፡፡ አለመታደል ሆኖብን እኛ ኢትዮጵያዊያኖች (Criticism) ን በ (Positive) የመመልከት ባኅሪ አልተቸርንም፣ ይልቁንም (Criticize) የሚያደርጉንን በበጎ መልኩ ከመመልከት ይልቅ (Defensive) መሆንን አልፎ ተርፎም እንደ ጠላት መፈረጅና አጋጣሚም ከተገኘ ወደማጥቃት መሸጋገሩን ስለምንመርጥ ስህተትን ለማረም ፈቃደኝነትንና ቅን መንፈስ ከማሳየት ይልቅ በስህተት ላይ ስህተትን እየደመርን ቁልቁል መውረድ እንመርጣለን፡፡ ስልሆነም ይህ ጽሁፍ <u>በጸሀፊው እይታ ስህተት የመሰለውን ለመተቆም እንጂ እንዱን አወድሶ ሌላውን ለማኮሰስ እንዳልሆነ በቅድሚያ እንዲታወቅለት ይፈልጋል</u>፡፡

ከላይ የጠቀስኩትን (Criticism) ን መቀበል እንደሚያዳግተን ለማስረጃ ይረዳ ዘንድ አንባቢያንን ለማሳሰብ የምወደው አንድ ነገር አለ ይሄውም ይሄንን ጽሑፍ በነፃው አለም ለሚገኙት አብዛኛዎቹ የድሕረ ገጽ አዘጋጆች በተለይ በብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ የሚጎበኙት ገናና ድሕረ ገፆች በሙሉ እልከዋለሁ ሰንቱ ነፃ ሀሳብ አስተናጋጅና እንደጠቀስኩትም (Criticism) ን እንዴት በንጹህ ህሊና መቀበል እንደሚችሉ አንባቢያን የወጣባቸውን ድሕረ ገፆች በመመልከት የራሳቸውን ግምት ይወስዱ ዘንድ በቅድሚያ አሳስባለሁ፡፡

ይህን ያክል ለመንደርደሪያ ከጠቆምኩ በኋላ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ለመተቸት እወዳለሁ፣ በመጀመሪያ (Reconciliation) እየተባለ ሰለሚለፈፍለት በመጠኑም ቢሆን ልተች እፈልጋለሁ (Reconciliation) ስላስፈላጊነቱ አጠያያቂ ባይሆንም፣ ሆኖም በመጸሐፍ ቅዱስ እንደተጠቀሰው "<u>ባይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ ሳታይ በጓደኛህ አይን ያለውን ጉድፍ ላውጣልህ አትበል</u>" የሚለው አባባል እየተተረጎመ ይመስላል፣ ይህንን ለማለት ያስገደደኝ በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑና በተቃዋሚነት ጎራ በተሰለፉት ድርጅቶች መሀከል አለመግባባትና ክፍተት እያለ ጸረ ኢትዮጵያ ከሆኑ ቡድኖች ጋር ተሰልፎ (Reconciliation) እያሉ ሰበካ የለበጣ ወይም ያዞ እንባ ማፍሰስ ይመስለኛል፣ እዚህ ላይ ልንረዳ የሚገባን ነገር ቢኖር ትላልቆቹና ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ባላቸው በሁለቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች መኻከል አለመግባባትና መሻከር እንዳለ ልንክደው የማንችለው ያደባባይ

ሚስጢር ነው፣ ይህ አንዱ ተጨባጭ ሲሆን ሌላውና በጣም የሚያሳዝነው ብሎም የሚገርመው ግን ከነዚሁ ሁለት ድርጅቶች አንደኛው የሆነው የአመለካከትና ያሰራር ልዩነት በመሀከላቸው ሳይኖራቸው ባንዳንድ ጥቃቅን ሁኔታዎች በመለያየታቸው ምክንያት በቻ እዚህ በ (Diaspora) ው ለሁለት ተከፍለው አንዱ አንዱን ሲወነጅልና ሲያጠቃ፣ ቃላቶች ሲወራወሩ መመልከቱ የተለመደ የየለቱ እይታ ሆኗል፣ ታዲያ እነዚህ ቡድኖች ከሌላው ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋር አብሮ መስራት ይቅርና ከራሳቸው ጋር መታረቅ ያልቻሉ መላው ኢትዮጵያን ሕዝብ ለማስተባበር (Reconciliation) እያሉ መስበክ ማሾፍ አይሆንም? እንዴት ነው ባለዛር ጠንቋይ ወንጌል ሊሰብክ የሚችለው? ተመልካች የፍረድ እላለሁ፡፡

እነዚህ በአመለካከት አንድ የሆኑ ነገር ግን ባልባሌ ምክንያቶች ሁለት የተከፈሉ ድርጅቶች የዛሬን አያርገውና በኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት ባላቸው አቋም፣ ለኢትዮጵያ ባላቸው ብሩህ ራእይ የተነሳ መላውን አለም እስከሚያስገርም ድረስ ይህ ነው የማይባል ሕዝባዊ ድጋፍ በማግኘት መመረጣቸው ሁላችንም የምናውቀው እውነታ ሆኖ ሳለ ዛሬ ግን  ለድል ካበቃቸው የኢትይጵያ ሕዝብ ፍላጎት ውጪ ተፃራሪ በሆነ መንገድ ሲጓዙ አካሄዳችሁን አሳምሩ፣ (አስተካክሉ) ተብለው ጥሪ ቢደረግላችው አሻፈረኝ በማለት የመረጣቸውን ኢትዮጵያዊ ወገናቸውን አሳዝነውታል፣ ለራሳቸው መግባባት አቅቷቸው ከሌላ ባእድ ነን ኢትዮጵያ የዛሬ መቶ አመት የተመሰረተች ሐገር ናት፣ እኛ ግን ኢትዮጵያዊያን አይደለንም ባዮች ጋር አብሮ መስራት ይቻላል እያሉ ዘጥ ዘጥ ሲሉ መመልከት አሳዝኖኛል ፣ ይህ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢያችን ናት ከኢትዮጵያ ተገንጥለን፣ ነፃ ወጥተን ፣ የራሳችንን መንግስት መመስረት እንፈልጋለን ከሚሉ ጸረ ኢትዮጵያ የግንጠላ ቡድኖች ጋር እየተሞዳሞዱ ኢትዮጵያዊውን ወገን የራሳቸው የሆነውን በኢትዮጵያ ሉአላዊነት የማያወላዳ አቋም ያላቸውን በማግለል አልፎ ተርፎም የአንድ ፓርቲ አባል ሆነው ሳለ በጥቃቅን ልዩነት የተነሳ ብቻ እርስ ብርስ እየተወነጃጀሉ እየተጋፉና እያገለሉ ዛሬም ሰለ ሕብረትና አንድነት ከኛ በላይ ደቀመዝሙር ላሳር ሲሉ ይደመጣሉ፣ (AFD) በመባል የሚታወቀውን ጸረ ኢትዮጵያ አፍራሽ ሰነድ አዝለው እኛ እናውቅላችኋለን አርፋችሁ ተቀመጡ ይሉናል፡፡ እግዚሀር ያሳያችሁ ኢትዮጵያዊ ከሆነው ድርጅት ጋር አብረው መስራት አይችሉም፣ እርስ ብርሳቸውም የአንድ ፓርቲ አካል ሆነው አበረው መሰራት አይችሉም፣ ግን OLF, ONLF, SNLF, ብለው እራሳቸውን ከሚጠሩት የተገንጠይ ቡድኖች ጋር ግን አብረው መስራት ይችላሉ ችግርም የለባቸው ፣ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት F, F ፎች በሙሉ ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል መቀበል አይደለም ስሙንም ለመጥራት የሚቀፋቸው ፣ ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ለመበተን ቆርጠው የተነሱ ፣ ታሪካችንን በመሰረዝና በመደለዝ የራሳቸው የሆነ ልብ ወለድ ጥላቻና ቂም የተሞላ ታሪክ በመሞነጫጨር አዲሱን ትውልድ ጸረ ኢትዮጵያ አመለካከት ይዞ እንዲያድግ ባለ በሌለ ጉልበታቸው ሲረባረቡ እያየን ተዋቸው የኛው ወገን ናቸው እያሉ ያፌዙብናል ፡፡ ዛሬ እነዚህ አፍራሽ ቡድኖች በአረብ ፣ በሻቢያ ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያን አንድነትና ብልጽግና ማየት ከማይፈልጉ የምራባውያን ሐገሮች በሚጣልላቸው ፍርፋሪ ልባቸው ያበጠ ለምኖ አዳሪዎችን እንኮኮ ብለው ሲዞሮ እያስተዋልን ነው፣ ፣ የነሱንም ጸር እትዮጵያ የሆነ ምናምን  (AFD) ን ወያኔ ይፈራዋል እያሉ ሊሰብኩን ይቃጣቸዋል ወያኔም ስራውን ያውቃልና (AFD) ን እንደሚፈራ  እና እንዳሳሰበው አድርጎ ይዘግብልናል፣ ለመሆኑ ይሂንን ድኩማን ድርጅት ያቋቋመው የሱው አበልጅ ሻቢያ አይደለምን? ወያኔስ ከመቼ ወዲህ ነው ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት

አሳቢ የተደረገው? (በነሱ አባባል (AFD) ለኢትዮጵያ የቆመ ነው ካልን) ወያኔ ለኢትዮጵያ ቢያስብ ነው ኤርትራን አስገንጥሎ ኢትዮጵያን ያለወደብ ያስቀረው? ወያኔ ለኢትዮጵያ ቢያስብ ነው በዘርና በጎሳ ከፋፍሎ ክልል ያቋቋመለን? ወያኔ ለኢትዮጵያ ቢያስብ ነው አንቀጽ 39 ሕገ መንግስቱ ላይ ያሰፈረለን? የወያኔን ሕገ መንግስት በመመርኮዝ አይደለም ይሄ ሁሉ ተገንጣይ እንዳሸን የፈላብንና ዛሬ በአረብ ሶልዲና በሻቢያ ተገንነት ኢትዮጵያን ካላፈረስኩ እያለ አፉን ሞልቶ አረፋ እስከሚደፍቅ ድረስ የሚፎክርብን? እና ወያኔ እራሱ የመሰረተውን (AFD) ን እንዴት አድርጎ ነው የሚፈራውስ ፣ የሚቃወመውስ? የወያኔ ተግባር ገና ከጥንሡ ኢትዮጵያን ማፈራረስና መገነጣጠል አይደለምን? ወይንስ ወያኔ ለኢትዮጵያ አንድነት የቆመ ነው ልንባል ይሆን? ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባ ይላል ያገራችን ሰው ፣ ወይስ እውነቱንና ሀቁን ማየት ተስኖናል?

እዚሁ ላይ ሌላ በሁለተኛነት ማከል የምፈልገው ነገር ቢኖር ፣ ማንም ግለሰብ ይሁን ድርጅት ከኢትዮጵያ እንዳማይበልጥ እነዚሁ እናውቅላችኋለን ባዮች የዘነጉት ስለመሰለኝ በመጠኑ ልተችበት እወዳለሁ ፣ ሁሌም ይሄንን ጸረ ኢትዮጵያ የሆነውን ሰነዳቸውን (Challenge) በተደረጉ ቁጥር ቃሊቲ ያሉትም መሪዎቻችን ይደግፉታል ይሉናል ፣ ያ ማለት ቃሊቲ ያሉት መሪዎቻችን ከሕዝብና ካገር በላይ ናቸው ለማለት ነው ወይንስ የቃለቲ መሪዎቻችን መለኮትነት ስላላቸው አይሳሳቱም ሊሉን ፈልገው ይሆን? እንደኔ እምነት ከሆነ ቃሊቲ ያሉት መሪዎቻችን አንድም ስለ ድኩማኑ (AFD) አያውቁም ወይንም ካወቁም የሚያውቁት <u>ሕብረት መሰረትን በሚል ቁንጽል አቀራረብ ብቻ ይመስለኛል</u> እንጂ ይህ ጦሰኛ ሰነድ በውስጡ ያለውን ስንክሳር አብጠርጥረው ያዩትና የሚያውቁት አይመስለኝም፣ እኛ በነፃነት ያለነው የምናውቀውን ያክል ግንዛቤ ኖሯቸው ከሆነም የደገፉት እነሱን እንደ ፍጹም ተመልክቼ እነሱ ካሉ ይሁን የምለው ጉዳይ የለኝም፣ እርግጥ ለሐገርና ለአንድነት ለነፃነት ሲሉ ቢታሰሩም እዚህ ላይ ተሳስታችኋል ተብለው ሊነገሩ ይገባል ፣ የሚያስተካክሉትም ከሆነ ሊያስተካክሉ የግድ ይላል ካልሆነ እነሱም እዚህ በዲያስፖራ እንዳሉት ሊዋጥልን ያልቻለውን ዋጡ የሚሉን ከሆነ ከነሱም ጋር በተፃራሪ የማልቆምበት ምክንያት አይታየኝም ፣ እንዲያውም ሀሳባቸው ያ ከሆነ ከነሱም ጋር ቢሆን በተቃዋሚነት ለመቆም የአንድ ሴኮንድ ጊዜም ማሰብ አያሻኝም፡፡ ይሄ ነው እንግዲህ ማንም ግለሰብም ይሁን ቡድን ከሐገር አይበልጥም ያልኩበት ምክንያት፡፡ እንግዲህ ከሕዝብ በላይ ላገር አዋቂና አሳቢ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ሊሆኑ እንዳማይችሉ መገንዘብ ይኖርብናል ፣ ካገር በላይ ማንም እንደማይበልጥ መገንዘብ ከተሳናችው ከሰልፉ ውጪ እንደሆኑ መረዳት ይኖርባቸዋል ፣ በዚህ አይነት አጓጉል መንገድ ከቀጠልን የዛሬው መንፈስ ነገ አምላክ ነኝ የማይልበት ምክንያት አይታየኝምና ስለሆነም “በንቁላሌ በቀጣሽኝ” የሚለው ተረት እንዳይተገበር ያስፈራኛል፡፡

ቸር ይግጠመን፣

በተባበረ ትግላችን እናሸንፋለን!!